# የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርት የዕውቅና አሰጣጥ መመሪያ

(መደበኛ ትምህርት)

ትምህርት ሚኒስቴር

ሰኔ 2004

አዲስ አበባ

የተሻሻለ

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ

## 1. መግቢያ

በኢ.ፌዲሪ የትምህርት ሚኒስቴር በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ 650/2001 አንቀፅ 97/2 እንዲሁም የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 30 በተሰጠው ስልጣን መሰረት የከፍተኛ ትምህርት አግባብነት እና ጥራትን ለማስጠበቅ ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## 2. የመመሪያው አስፈላጊነት

ይህን መመሪያ ማውጣት ያስፈለገው የሚከተሉትን ዓላማዎች ለማሳካት ነው።

1) መንግሥት በተለይ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ የስልጠና ዘርፎች ያስቀመጠውን አቅጣጫ መሰረት በማድረግ ብቁ፣ ተወዳዳሪና ገበያው የሚፈልገውን የሰው ሃይል በማፍራት የታቀደውን ልማት ቀጣይነት ማረጋገጥ፣
2) የትምህርትና ስልጠና ጥራት የማረጋገጥ ሂደት ውጤትን፣ ሂደትንና ግብዓትን ማዕከል በማድረግ የሚሰራበትን የተጠናከረ ስርዓት መዘርጋት፣
3) ተቋማት ጥራት ያለው ትምህርትና ስልጠና ለመስጠት ያላቸውን ብቃትና ዝግጁነት በየጊዜውና ቀጣይነት ባለው መልኩ እየፈተሹና እያጠናከሩ መሄድ የሚችሉበትን ስርዓት መዘርጋት፣

## 3. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርት የዕውቅና አሰጣጥ መመሪያ ሰኔ 2004" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 4. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ፡-

1) "አዋጅ" ማለት የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 ነው።
2) "ሚኒስቴር" ማለት የትምህርት ሚኒስቴር ነው።

3) "የከፍተኛ ትምህርት" ማለት በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 8 የተመለከተውን ትርጉም ይይዛል።
4) "ኤጀንሲ" ማለት የትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ ነው።
5) "ተቋም" ማለት የከፍተኛ ትምህርት የሚሰጥ የግል ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ አካል ነው።
6) "መደበኛ ትምህርት" ማለት በቀን እና በማታ የተቀመጠውን የክሬዲት አወር እና የስልጠና ዘመን ርዝማኔ በመጠበቅ የሚሰጥ ትምህርት ነው።
7) "የዕውቅና ፈቃድ" ማለት ትምህርትና ሥልጠና ለመጀመር በአዋጁ መሰረት ለተቋም የሚሰጥ የስራ ፈቃድ ነው።
8) "የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት" ማለት ትምህርትና ስልጠና እንዲቀጥል በአዋጁ መሰረት ለተቋም የሚሰጥ የእድሳት ፈቃድ ነው።
9) "የማስተማሪያ መጽሐፍ" ማለት አንድ ትምህርት (ኮርስን) ለማስተማር የሚረዳ ሰፋ ያለና ዝርዝር መረጃዎችን የያዘና ተማሪዎች ትምህርቱን እንዲጨብጡ የሚረዳ መፅሐፍ ነው።
10) "የማጣቀሻ መጽሐፍ" (Reference book) ማለት ሊሰጥ ለታሰበው ትምህርት (ኮርስ) የመረጃ ምንጭ ሆኖ የሚያገለግል መጽሐፍ ነው።
11) "ሳይንቲፊክ ጆርናል" ማለት ሳይንሳዊ የምርምር ውጤቶች የሚታተሙበት ታዋቂ መጽሔት ነው።
12) "የማታ ትምህርት" ማለት በማታው እና በተጨማሪም በሳምንቱ የመጨረሻ ቀናት የሚሰጥ የትምህርት ፕሮግራም ማለት ነው።
13) "ካምፓስ" ማለት ተቋሙ ራሱን ችሎ የእውቅና ፈቃድ የጠየቀበት የአንድ ዋና ተቋም ቅርንጫፍ ማለት ነው።

## 5. የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ጸድቆ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በማንኛውም ተቋም ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

## 6. ዝርዝር መመዘኛዎች

የዚህን መመሪያ ማስፈጸሚያ ዝርዝር መመዘኛዎችና የጥራት ደረጃዎች ኤጀንሲው ያወጣል።

# ክፍል ሁለት
# የእውቅና እና የእውቅና ፈቃድ ዕድሳትን ለማስተናገድ የሚያገለግሉ መሰረታዊ ነጥቦች
# የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርት (92170)

## 7. መርሆዎች

በዲግሪ ፕሮግራም ትምህርትና ስልጠና ለመስጠት ተፈጻሚነት ያላቸው የአዋጁ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በተለይም

1) ማንኛውም ተቋም ተማሪዎችን የሚቀበልበት ሥርዓት በሃይማኖት፣ በብሔር በፆታና በመደብ ልዩነት የማይደረግበት ይሆናል።
2) ትምህርቱ ወይም ሥልጠናው ከሃይማኖት ነፃ የሆነ ወይም ሴኩላር መሆን ይኖርበታል፤
3) በሌሎች ቋንቋዎች ትምህርት መስጠት ወይም ጥናት ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር የማንኛውም ተቋም የማስተማሪያ ቋንቋ እንግሊዝኛ ይሆናል።
4) ተቋሙ የዕውቅና ፈቃድ ወይም የዕውቅና ፈቃድ እድሳት የሚጠይቅባቸው የትምህርትና ስልጠና መስኮች ኢኮኖሚው የሚፈልገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል ይሆናል፤
5) ተቋሙ ማስተማር የሚችለው የዕውቅና ፈቃድ እና የዕውቅና ፈቃድ እድሳት በተሰጠው የትምህርት ዓይነትና መጠን ልክ ብቻ ይሆናል፤
6) የተቋሙ ስያሜ በአዋጁ ለደረጃው የተቀመጠውን መስፈርት የሚመጥን ይሆናል፤ በኤጀንሲውም ይረጋገጣል፤
7) ተቋሙ የሚያካሂደው የምርምር ሥራ የአገሪቱን እድገትና ልማት የሚያፋጥን፣ የሚያስቀጥልና ችግር ፈቺ መሆን ይኖርበታል፤
8) በማታው መርሃ-ግብር የሚሰጥ ትምህርት ራሱን እንዳስፈላጊነቱ የቻለ የእውቅና ፈቃድ ይኖረዋል፤ የሚሉትን መሰረታዊ መርሆዎችን የተከተለ ይሆናል፤
9) ለማንኛውም ተቋም የሚሰጠው የእውቅና ፈቃድ በካምፓስ ደረጃ ይሆናል።

## 8. የተማሪዎች ቅበላ መስፈርት

ማንኛውም ተቋም ተማሪዎችን የሚቀበለው በአዋጁ አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ (1) ፣ 3 (ሀ) እና (ሐ) በተደነገገው መሰረት

1) የመሰናዶ ትምህርት ያጠናቀቁትንና ሚኒስቴሩ የሚያስቀምጠውን የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና የማለፊያ ነጥብ የሚያሟሉትን፣
2) በውጭ አገር የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን አጠናቀው በኤጀንሲው የአቻ ግምት የተሰጣቸውን፣
3) ከቴክኒክና ሙያ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የመሸጋገሪያ መመሪያ ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች ያሟሉትን፣
4) ተቀባይነቱ የተረጋገጠ ሌላ ዲግሪ ያላቸውን፣
5) ሚኒስቴሩ የሚያወጣውን መመሪያ የሚያሟሉ ጎልማሶችን

ይሆናል።

## 9. የአካዳሚክ ዘመን

1) አንድ የአካዳሚክ ዘመን የመደበኛ የቀን ፕሮግራም ሁለት ሴሚስተሮች እና አንድ ክረምት ሊኖሩት ይችላል።
2) አንድ የአካዳሚክ ዘመን እያንዳንዳቸው ከ15 የማይበልጡ ክሬዲት አወር ያሉት ሁለት ሴሚስተሮች እና ከ 6 ክሬዲት አወር የማይበልጥ የክረምት ፕሮግራም ይኖረዋል።

## 10. የተማሪዎች ቅበላ

የአዲስ ተማሪዎች የቅበላ ጊዜ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ይሆናል። ከዚያ በላይ ከሆነ ተቋሙ የሚጠበቀውን መስፈርት በማሟላት ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ከኤጀንሲው ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል።

## 11. ትምህርቱ ወይም ሥልጠናው የሚሰጥበት ህንጻና ከባቢ ሁኔታ

1) ተቋሙ ትምህርቱን ወይም ሥልጠናውን የሚሰጥበት ሕንፃና ግቢ በተቋሙ በግል ንብረትነት የተያዘ ወይም በማናቸውም በሕግ ፊት ሊጸና በሚችል ውል ለ5 ዓመታት እንዲያገለግል በኪራይ የተያዘ መሆኑ፤

2) መማሪያው ሕንጻና ግቢው ለመማር ማስተማር ምቹ እና መማር ማስተማሩን ወይም የተማሪዎችና የመምህራን ጤንነት ለሚያውኩ ሁኔታዎች ባልተጋለጠ ከባቢ መሆኑ፣
3) ተቋሙ ያለበት የመሬት አቀማመጥ ለጎርፍ፣ ለከባድ ንፋስ፣ ለፍሳሽና ሌሎች አደጋዎች ያልተጋለጠና ምቹ የመኪና መንገድ ያለው መሆኑ፤
4) ለተቋሙ ሠራተኞችና ተማሪዎች የተሰሩ በቂ የመጸዳጃ ክፍሎች፣ የመጀመርያ የሕክምና እርዳታ መስጫ ማዕከልና የጊዜ ማሳለፊያና መዝናኛ ክበቦች ያሉት መሆኑ እና
5) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቁ ሆኖ ተቋሙ የቦታ ለውጥ ከማድረጉ በፊት በኤጀንሲው ለመማር ማስተማሩ ሂደት አመቺ መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል።

# 12. ክፍያ

የዕውቅናና የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት አገልግሎት ክፍያን በተመለከተ በመንግሥት በጸደቀ ተመን መሰረት ይሆናል።

# 13. ስለ ዕውቅናና ዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት አስፈላጊነት

የግል ተቋምን ለማቋቋም፣ ደረጃውን ለማሳደግ፣ ለመለወጥ ወይም ዕውቅና በተሰጠው ለመቀጠል ወይም አዲስ የስልጠና መስክ ለመክፈት የሚፈልግ ማንኛውም ተቋም በአዋጁና በዚህ መመሪያ የዕውቅና ፈቃድ ሳያገኝ የከፍተኛ ትምህርት ሊሰጥ አይችልም።

# ክፍል ሶስት

## የዕውቅና ፈቃድ አሰጣጥ መገምገሚያ መስፈርቶች

## 14. የዕውቅና ፈቃድ አገልግሎት ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

የግል ተቋምን ለማቋቋም፣ ደረጃውን ለማሳደግ ወይም ለመለወጥ ወይም ተጨማሪ ካምፓስ ለመክፈት ወይም አዲስ መርሃ-ግብር/ፕሮግራም ለመክፈት ወይም በተፈቀደለት ፕሮግራም የተማሪዎች ብዛት ለመጨመር የሚፈልግ ማንኛውም ተቋም አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን የያዘ የዕውቅና ፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻ ለኤጀንሲው ማቅረብ ይኖርበታል። የሚቀርበው ማመልከቻ በአዋጁ አንቀጽ 75 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆኖ

1) ለተቋሙ ደረጃ የሚመጥን አካዳሚያዊና አስተዳደራዊ አደረጃጀት፣
2) ተቋሙ ለሚያቀርበው የስያሜ ደረጃ  አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን እና
3) የሕንጻ የይዞታ ማስረጃ ወይም የአምስት ዓመት የኪራይ ውል ማቅረብ ይኖርበታል።

## 15. የዕውቅና ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

በአዋጁና በዚህ መመሪያ መሰረት ትምህርትና ሥልጠና ለመስጠት የተዘጋጀ ተቋም ተማሪዎችን ተቀብሎ ማስተማር የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው።

1) ተቋሙ በአንድ የትምህርት ዘመን በአንድ የስልጠና መስክ ከተፈቀደለት ቁጥር በላይ ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማሰልጠን ከፈለገ የሚጠበቀውን መስፈርት በማሟላት ትምህርትና ስልጠና ከመጀመሩ በፊት ከኤጀንሲው ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል።

2) የተቋሙ አመራርና አደረጃጀት

ሀ) በዲግሪ ደረጃ ሥልጠና ለመስጠት የሚያስችል፣ ግልጽና የመማር ማስተማር፣ የምርምር እና የማህበረሰብ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችለው አደረጃጀት (Senate/Academic Commission, Department council...) ሊኖረው ይገባል።

ለ) ለዲግሪ ፕሮግራም ራሱን የቻለ አደረጃጀትና የአስተዳደር ስርዓት ያለው፣

ሐ) የተቋሙ በጀት ለሚሰጠው ግልጋሎት በቂና አስተማማኝ የሆነ፣

መ) በሚፈለገው ብዛትና ዓይነት በስልጠናውና በአገልግሎት ስራ ላይ የተሰማሩ በቂ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች እና

ሠ) የእያንዳንዱን ክፍልና ሰራተኞች የሥራ ድርሻ በጽሁፍ በተደገፈ ሰነድ የተቀመጠ መሆን ይኖርበታል።

## 3) መምህራንን በተመለከተ

ሀ) በእያንዳንዱ የስልጠና መስክ ለአንድ ባች ተማሪ አብይ ኮርሶችን (Major Courses) የሚሰጡ ለመጀመሪያ ዓመት ፕሮግራም ለማስጀመር ቢያንስ 2 ሁለተኛ ዲግሪ እና 1 የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው መምህር፣ በሁለተኛው ዓመት 2 ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው እና 1 የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው እንዲሁም በሶስተኛው ዓመት 3 ሁለተኛ ዲግሪ እና 1 የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው መምህር ሊኖረው ይገባል።

ለ) በተራ ቁጥር "ሀ" የተቀመጠው የመምህራን ብዛትና ስብጥር ከስልጠና ጊዜ ርዝማኔ ጋር ተያይዞ ከሚኖረው የተማሪ ባች ጋር አብሮ የሚያድግ ይሆናል።

ሐ) የእያንዳንዱ መምህር ሳምንታዊ ጫና በመደበኛው የቀን ክፍለ ጊዜ ከ12 ክሬዲት አወር ያልበለጠ ይሆናል፣

ሠ) መምህራን ያላቸውን ክህሎት የሚያሳድጉበት ስልጠና የሚወስዱበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፣

ረ) አብይና ደጋፊ ኮርሶችን የሚያስተምሩ መምህራን ሁሉም የማስተርስና ከዚያ በላይ የትምህርት ደረጃ ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፣

ሰ) ተቋሙ ምጣኔው 33 ከመቶ ያልበለጠ ጊዜያዊ መምህራን ሊኖሩት ይችላል፣

ሸ) የመምህር ተማሪ ጥምርታ እንደ ፕሮግራሙ የሚለያይ ሆኖ በአማካይ የተማሪ መምህር ጥመርታ 1:30 ሊሆን ይገባል፣

ቀ) ተቋሙ በቋሚነት ለቀጠራቸው መምህራን አስፈላጊውን መረጃ ማቅረብ ይጠበቅበታል፣

በ) ከውጭ የተገኘ ዲግሪ ከሆነ የአቻ ግመታ ተሰርቶ መቅረብ አለበት፣

ተ) የተቋሙ መምህራን ምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት የሚሰጡበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፣

ቸ) በአንድ ከተማ ውስጥ ለሚገኙ ካምፓሶች በአንቀጽ 13.3 በንዑስ አንቀጽ “ሐ” የተቀመጠውን ባገናዘበ መልኩ የእውቅና ጥያቄ ይስተናገዳል።

## 4) የስርዓተ ትምህርት ቀረጻ ሂደት እና ተገቢነት

ማንኛውም ተቋም ለሚሰጠው ትምህርትና ስልጠና በአግባቡ የተቀረጸ ስርዓተ ትምህርት ያለው ሆኖ፡-

ሀ) የትምህርት ዓይነቱ ከአገር ፍላጎት ጋር የተገናዘበ፣ አግባብነት ያለው፣ ሰልጣኙን ለስራ የሚያዘጋጅና ችግር ፈቺ ዜጋ የሚያፈራ፤

ለ) የትምህርት ዓይነቱ ዓላማዎችና የምሩቃን ፕሮፋይል በግልጽ የተቀመጠ፤

ሐ) ለእያንዳንዱ ኮርስ የተሟላ ዓላማ፣ መግለጫ (course description)፤ የማስተማሪያና የምዘና ዘዴዎችን፤ የውጤት አሰጣጥ የመማሪያ እና ማጣቀሻ መጽሐፍት ዝርዝር የያዘ፣

መ) እንደትምህርቱ ዓይነት በቂ ቁጥር፤ ዓይነትና አመጣጠን ያላቸው አብይ፣ ደጋፊና መሰረታዊ ኮርሶች፤

ሠ) የስርዓተ ትምህርቱን አፈጻጸም የሚከታተል ተገቢ አደረጃጀት፤

ረ) ትምህርቱና ስልጠናው ሴሚስተርን መሰረት አድርጎ የሚሰጥ መሆኑ፤

ሰ) በየሴሚስተሩ (16 ሳምንት) በመደበኛ መርሃ-ግብር የሚሰጠው የክሬዲት አወር መጠን ከ18 ክሬዲት አወር የማይበልጥ እና አስገዳጅ በሆኑ ሁኔታዎች የክሬዲት አወር መጠኑ በተቋሙ የአካዳሚክ ኮሚሽን ወይም ሴኔት ውሳኔ በቃለ ጉባዔ ተደግፎ እስከ 21 ክሬዲት አወር ከፍ ሊል የሚችል መሆኑን፣

ሸ) ለዲግሪ ፕሮግራሞች መሰጠት ከሚገባው የክሬዲት አወር መጠን አብይ ኮርሶች ከጠቅላላው ክሬዲት አወር በአማካይ ከ66-76 በመቶ ያላነሰ ድርሻ መኖሩን የሚያሳይ እና

ቀ) አዲስ የስልጠና መስክ ለመክፈት የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት፣ በዐውደ ጥናት የተደገፈና የባለድርሻዎችን አስተያየት ያካተተ መረጃ መቅረብ ይኖርበታል።

## 5) ቤተ-መጻሕፍት እና የቤተ መጻሕፍት ግብዓቶች

ሀ) አጠቃላይ የተማሪውን ቁጥር ቢያንስ 25 ከመቶ በአንድ ጊዜ ማስተናገድ የሚችል እና በተማሪ 1.5 ካ.ሜ የተመጠነ የቦታ ስፋት ያለው፣

ለ) በቂ ብርሃን ያለውና አየር ማስገባት የሚችል፣

ሐ) በኢንሳይክሎፔዲያ፣ በመዝገበ ቃላት፣ በፒሪዮዲካልስ፣ ጋዜጦች ወዘተ. የተሟላ፤

መ) የኢንተርኔት አገልግሎት ያለው፣

ሠ) ቢያንስ እስከ ምሽቱ ሁለት ሰዓት ድረስ ቅዳሜና እሁድን ጨምሮ አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑን፤

ረ) በሙያው በቂ የትምህርት ዝግጅትና ልምድ ያለው የቤተመጻሕፍት ባለሙያና ረዳቶች ያሉት፤

ሰ) ከትምህርቱ ጋር አግባብነት ያላቸው  የቅርብ ጊዜ እትም የሆኑ የመማሪያና የማጣቀሻ መጻሕፍትና ሳይንሳዊ ጆርናሎች ያሉት እና

ሸ) ተቋሙ በኢ-ላይብራሪ የተደራጀ ከሆነ የኤሌክትሮኒክ መጽሐፍትና ጆርናሎች፤ እንደታተሙ መጻሕፍትና ጆርናሎች ሊቆጠሩ የሚችሉ ሆነው ተቋሙ ለዚህ አገልግሎት የሚውሉ ኮምፒዩተሮች ያሉት

ሊሆን ይገባል፡፡

## 6) የመማሪያ ክፍሎች

ሀ) በአንድ ተማሪ 1.2 ሜትር ካሬ ምጣኔ ለተማሪዎቹ እይታና ለመስማት በሚቻልበት ሁኔታ ሊሆን ይገባል።

ለ) ከላይ በተራ ቁጥር “ሀ” የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ ባች የሚኖረው የተማሪ ብዛት ከ60 በላይ ሊሆን የሚችለው ከላይ በአንቀጽ 15.1 መሰረት ተጨማሪ ሴክሽን እንዲቀበል ሲፈቀድ ብቻ ነው።

ሐ) የመማሪያ ክፍሎች በቂ ብርሃንና ቬንትሌሽን ያላቸው፣ ደረጃቸውን በጠበቁ ቁሳቁሶች የተደራጁ እና ለመማር ማስተማር ሂደት ምቹ የሆኑ ሊሆን ይገባል፡፡

## 7) ቢሮዎችን በተመለከተ

በተገቢው ቁሳቁስ የተደራጁ ለእያንዳንዱ የትምህርት ክፍል ኃላፊ፣ ለመምህራንና በተቋሙ ድርጅታዊ መዋቅር መሠረት ለሌሎች የሥራ ክፍሎች የሚያገለግሉ ቢሮዎች ሊኖሩ ይገባል።

## 8) የቤተ-ሙከራ፣ የዲሞንስትሬሽን፣ የወርክሾፕ ክፍሎች እና ግብዓቶች፣

ሀ) በተገቢው ግብዓቶች የተደራጁ በተማሪ 3.0 ካሬ ሜትር ቤተሙከራና የዲሞንትሬሽን ክፍል፣ 2.2 ካሬ ሜትር የቋንቋ ቤተሙከራ፣ 5.0 ካሬ ሜትር የድሮዊንግ ክፍል እና 6.0 ካሬ ሜትር ስፋት ያለው ወርክሾፕ፣

ለ) ለቤተሙከራ፣ ወርክሾፕ እና ዲሞንስትሬሽን ክፍሎች ከሥልጠናው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ረዳት ወይም ቴክኒሺያን እና

ሐ) ለሕክምናና የጤና ሣይንስ ፕሮግራሞች ልምምድ ከሚካሄዱባቸው ሆስፒታሎች ወይም ጤና ጣቢያዎች ጋር ሊያሰራ የሚችል መረጃ ሊኖር ይገባል፡፡

መ) ለተግባር ኮርሶች በአንድ ቤተሙከራ፣ ወርክሾፕ፣ ወዘተ የተማሪዎች ቁጥር ከ25 መብለጥ የለበትም።

## 9) የኮምፒውተር ማዕከሎች

ሀ) በኮምፒውቲንግ ሳይንስ፣ በማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና ተዛማጅ ትምህርቶች ሥልጠና የሚያካሂድ ተቋም ለኔትወርኪንግና እንደየስልጠና መስኩም ለጥገና ጭምር የሚያገለግሉ ወርክሾፖችን፣

ለ) ከሰርቨር ጋር እና እርስ በእርስ የተገናኘ (Server based network) እና የኢንተርኔት አገልግሎት የሚሰጥ የኮምፒውተር ማዕከል እና

ሐ) ለሌሎች የትምህርት ዓይነቶች መሰረታዊ የኮምፒውቲንግ ኮርሶችን ለመስጠት በተመሳሳይ መልኩ የተማሪዎችን ቁጥር ግምት ውስጥ ያስገባ የኮምፒውተር ማዕከላትን

ማደራጀት ይጠበቅበታል።

### 10) ፖሊሲዎች ደንቦችና መመሪያዎች

ማንኛውም የእውቅና ፈቃድ ጥያቄ የሚያቀርብ ተቋም በአግባቡ የተዘጋጁና የተሟሉ የሚከተሉትን ደንቦች ማቅረብ አለበት።

ሀ) አካዳሚክ ደንብ (የተማሪ ቅበላን፣ ምዝገባን፣ መልሶ መቀበልን፣ የትምህርት ጊዜን ኮርሶችን፣ የሴሚስተር ጫናን፣ ምዘናንና ለምረቃ የሚያበቁ ሁኔታዎችን) ፣

ለ) ክፍያንና የተመላሽ ገንዘብ አመላለስ፣

ሐ) የመምህራን የቅጥር ሥርዓት፣ መብትና ግዴታ፣

መ) የተማሪዎች መብትና ግዴታ፣

ሠ) የተማሪዎች ጋይዳንስና ካውንስሊንግ እና

ረ) የድጋፍ ሰጪና የአስተዳደር ሠራተኞች የቅጥር፣ ዕድገት፣ ስንብት፣ ወ.ዘ.ተ ደንቦች ማቅረብ አለበት፡፡

### 11) የቦታ ስፋት ደረጃዎች

አንድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሕንፃ ሲገነባ ወይም ሲከራይ ለአንድ ተማሪ የሚያስፈልገውን የቦታ መጠን ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት።

## 16. የማታ ትምህርትን በተመለከተ

1) ማንኛውም በማታ መርሃግብር ለማሰልጠን የእውቅና ፈቃድ ጥያቄ የሚያቀርብ ተቋም ለመደበኛው የተቀመጠውን መስፈርት አሟልቶ ሲገኝ ተማሪዎችን ተቀብሎ ማሰልጠን ይችላል።
2) አንድ ተቋም በመደበኛው የቀን ክፍለጊዜ የሚያስተምረውን የስልጠና መስክ በተፈቀደለት ካምፓስ ኤጀንሲውን በማሳወቅ ብቻ በማታው ክፍለ ጊዜ ማስተማር ይችላል።
3) በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተቀመጠው ቢኖርም የስልጠና መስኩ በመደበኛው የቀን ክፍለ ጊዜ የማይሰጥ ከሆነ ወይም ከተፈቀደለት ካምፓስ ውጭ ማስተማር ከፈለገ ለማታው ክፍለ ጊዜ የእውቅና ፈቃድ ጥያቄ ለኤጀንሲው ማቅረብ ይኖርበታል።
4) በማታው ክፍለ ጊዜ በአንድ ሴሚስተር እስከ 12 ክሬዲት አወር እንዲሁም በክረምት እስከ 6 ክሬዲት አወር ማስተማር ይችላል።

5) የሕክምና እና የጤና ሳይንስ ፕሮግራሞች በማታውም ሆነ በሳምንቱ መጨረሻ ባሉት ቀናት ማስተማር አይፈቀድም።
6) በማታው መርሃ-ግብር የሚሰጥ ትምህርት የሚወስደው የስልጠና ጊዜ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተቀመጠውን መሰረት ባደረገ መልኩ ይሆናል።

## 17. የዕውቅና ፈቃድ ስለመስጠት

1) ኤጀንሲው በአንቀፅ 15 ንዑስ አንቀፅ 1-11 የተቀመጡ መመዘኛዎች መሟላታቸውን ገምግሞ በማረጋገጥ የዕውቅና ፈቃድ ይሰጣል።
2) ተቋሙ የዕውቅና ፈቃዱን በወሰደበት ሴሚስተር ተማሪዎችን መመዝገብ ካልቻለ ምዝገባ ከመጀመሩ በፊት ለኤጀንሲው ማሳወቅ ይኖርበታል።

# ክፍል አራት
# የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት አሰጣጥ
# መገምገሚያ መስፈርቶች

## 18. የዕውቅና ፈቃድ እድሳት አገልግሎት ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

ትምህርትና ስልጠና ሲሰጥ የቆየ ተቋም ትምህርትና ስልጠናውን ለመቀጠል አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን የያዘ የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት ማመልከቻ ለኤጀንሲው ማቅረብ አለበት፡፡ ማመልከቻው በክፍል ሶስት አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 1፣ 2 እና 3 የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆኖ፡-

1) የትምህርት ግብዓቶችና መገልገያዎች አሁን ያሉበትን ደረጃ የሚገልጽ ሪፖርት፣
2) የተቋሙ የአካዳሚክ፣ የቴክኒክና የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ዝርዝር፣
3) በየዓመቱ ተቋሙ በሚሰጠው በእያንዳንዱ የትምህርት መስክ የተመዘገቡ ተማሪዎች ዝርዝር፣
4) በኦዲተር የተመረመሩ የመጨረሻዎቹን ሁለት ዓመታት የሂሳብ ሪፖርቶች፣
5) የስድስት ወር እና ዓመታዊ የአፈጻጸም ሪፖርት፣
6) የጥራት ማጎልበት ዩኒት ዓመታዊ ሪፖርት፣
7) የምርምርና ስርፀት የስራ ክንውን ሪፖርት እና
8) ተቋሙ ካለው የፕሮግራሞች ዓይነት አኳያ ለትምህርት ጥራት መሻሻል በያዘው የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ መሰረት መዋዕለንዋይ እያፈሰሰ መሆኑን የሚያሳይ ሪፖርት መቅረብ አለበት።

## 19. የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

1) የተቋሙ አደረጃጀትን በተመለከተ

በአንቀፅ 15 ንዑስ አንቀፅ 2 የተዘረዘሩት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው ተቋሙ በአደረጃጀቱ ላይ ያደረጋቸው ለውጦችን/መሻሻሎችን የያዘ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል።

2) **የመምህራን ብዛትና ስብጥር**

በአንቀፅ 15 ንዑስ አንቀፅ 3 የተዘረዘሩት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው፡-

ሀ) ተቋሙ ለመጀመሪያ ጊዜ የእውቅና ፈቃድ እድሳት ጥያቄ ሲያቀርብ በየሙያው ቢያንስ 3 ሁለተኛ ዲግሪ እና 1 የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው መምህር ሊኖረው ይገባል፣ ሆኖም እንደየስልጠና መስኮቹ የቆይታ ጊዜ በሚኖረው የተማሪ ባችና ሴክሽን መሰረት ብዛትና ስብጥሩ የሚያድግ ይሆናል።

ለ) የተቋሙ መምህራን ምርምር የሚሰሩበትና የሕብረተሰብ አገልግሎት የሚሰጡበት ስርዓት ተጠናክሮ ሊተገበር ይገባል።

ሐ) ተቋሙ ለሁለተኛ ጊዜ የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት ሲጠይቅ እንዲያሟላ ከሚጠበቀው የመምህራን ቁጥር ውስጥ ቢያንስ አንድ ፒ.ኤች.ዲ ያለው መምህር እንዲኖረው ይጠበቃል። ሆኖም በአገሪቱ ውስጥ ያለውን በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ግምት ውስጥ በማስገባት የስልጠናና የምርምር ተግባራትን በተፈለገው የጥራት ደረጃ ማካሄድ የሚያስችል የተጠናከረ የመምህራን ልማት ፕሮግራም አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል።

3) **ስርዓተ ትምህርትን የማሻሻል ሂደት**

በአንቀፅ 15 ንዑስ አንቀፅ 4 የተዘረዘሩት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው ተቋሙ በሥርዓተ ትምህርት ላይ ያደረጋቸውን ለውጦች የያዘ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል።

4) **ቤተ-መጻሕፍትና የቤተ መጻሕፍት ግብዓቶች**

በአንቀፅ 15 ንዑስ አንቀፅ 5 የተዘረዘሩት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው ተቋሙ በቤተ መጻሕፍት አደረጃጀትና የመጻሕፍት ክምችት ላይ ያደረጋቸውን ለውጦች የያዘ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል።

5) **ፊዚካል ግብዓቶች**

በአንቀፅ 15 ንዑስ አንቀፅ 6፣ 7፣ 8 እና 9 የተዘረዘሩት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው ተቋሙ በፊዚካል ግብዓቶች ላይ ያደረጋቸውን ለውጦች የያዘ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል።

6) **ደንቦችና መመሪያዎች**

በአንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 10 የተዘረዘሩት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው ተቋሙ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ ስለመሆናቸው የሚገልፅ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል።

7) **ግለ-ግምገማ**

ሀ) በተቋም ደረጃ የግለ ግምገማ ሰነድ በማቅረብ ኦዲት የተደረገ ተቋም የእውቅና ፈቃድ እድሳት ጥያቄ ከማቅረቡ ከአንድ ዓመት በፊት በፕሮግራም ደረጃ የግለ ግምገማ ሰነድ ማቅረብ ይኖርበታል።

ለ) ተቋማዊ ኦዲት ያልተካሄደበት ማንኛውም ተቋም የእውቅና ፈቃድ እድሳት ጥያቄ ከማቅረቡ ከአንድ ዓመት በፊት ተቋማዊ የግለ ግምገማ ሰነድ ማቅረብ ይኖርበታል።

## 20. የመማር ማስተማር ሂደት ግምገማ

በተቋሙ የሚካሄዱት የመማር ማስተማር፣ የምርምርና የማህበረሰብ አገልግሎት እንቅስቃሴዎች በተጨባጭ ይገመገማሉ፣

1) **የመማር ማስተማር ሂደት**

ሀ) የተለያዩ አሳታፊና ተማሪ ተኮር የመማርያ ዘዴዎችን መጠቀሙ፣

ለ) በተግባር የተደገፈ ትምህርት መሰጠቱ፣

ሐ) የታቀደ አካዳሚክ የማማከር ስራ መሰራቱ፣

መ) የመምህራን ግምገማ ስርዓትና አፈጻጸም እና የተወሰዱ የእርምት እርምጃዎች በመረጃ የተደገፉ መሆኑን፣

ሠ) የኮርስ ሽፋንና ስርዓተ ትምህርቱን መሰረት ያደረገ ስለመሆኑ እና

ረ) የተቋሙ መምህራን ሙያዊ ስነምግባር መከታተያ ስርዓት የሚታዩ ይሆናል።

2) **ምዘናና የምዘና ስርዓት**

ሀ) ፈተናዎች የሚወጡበት፣ የሚገመገሙበትና የሚጸድቁበት የአስተዳደር ስርዓት ፣

ለ) ተከታታይ የምዘና ስርዓት፣

ሐ) ወጥ የሆነ የውጤት አሰጣጥ ስርዓት እና

መ) ምዘናው በስርዓተ ትምህርቱ ከተቀመጡት ዝርዝር ዓላማዎች ጋር አብሮ የሚሄድ መሆኑ ይታያል።

3) ለስርዓተ ትምህርቱ ወቅታዊ የሆነ የማሻሻል ስርዓት ስለመኖሩ፣

4) ለተማሪዎች የድጋፍ አገልግሎት፣

5) የጥናትና ምርምር እና የፕሮጀክት ስራዎች

ሀ) የመመረቂያ ጽሁፍ ወይም የፕሮጀክት ስራ የማማከር ሂደት፣

ለ) የጥናትና ምርምር ፕሮፖዛል አዘገጃጀት፣ ግምገማና አጸዳደቅ ስርዓትና የበጀት አጠቃቀም ስርዓት እና

ሐ) የጥናትና ምርምር ስርፀት እንዲሁም እንዳስፈላጊነቱ የገበያ ትስስር ስርዓት ስለመኖሩ

ይታያል።

6) የመምህራን ልማት

ሀ) የመምህራን ልማት እቅድና አፈጻጸም እና

ለ) መምህራንን ከአዳዲስ ቴክኖሎጂ እና እውቀቶች ጋር የማስተዋወቅና የማብቃት ስራ ስለመተግበሩ ይታያል።

7) ቅጥርና እድገት

የመምህራንና የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች የቅጥርና እድገት መመዘኛዎች እና አተገባበራቸው የሚታዩ ይሆናል።

## 21. የውጤት ግምገማ

ተቋሙ በመማር ማስተማር፣ በምርምርና በማህበረሰብ አገልግሎቶች ያስገኛቸው ውጤቶች ይገመገማሉ። በዚህ መሰረት ተቋሙ፦

1) ያከናወናቸው ችግር ፈቺ የምርምር ስራዎች፣ የቴክኖሎጂ ፈጠራና ሽግግሮች እና የታተሙ ጽሁፎችን፣
2) ለማህበረሰቡ ያበረከተው አገልግሎቶችን፣
3) ስራ የመፍጠር ብቃትና በኢንዱስትሪው ተቀጣሪ የሆኑ ምሩቃንን ማፍራቱ እና
4) ያካሄደው የቀጣሪዎች የእርካታ ዳሰሳ ውጤት የሚታዩ ይሆናል።

## 22. የእውቅና ፈቃድ እድሳት ስለመስጠት

በአንቀጽ 15፣ 18 እና 19 የተዘረዘሩት መሟላታቸውን በማረጋገጥ ኤጀንሲው የእውቅና ፈቃድ እድሳት ይሰጣል።

## 23. ሌሎች የአዋጁን ድንጋጌዎች በተመለከተ

የእውቅና ፈቃድ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ፣ የዕውቅና ፈቃድ ስለመከልከል፣ የእውቅና ፈቃድ እና የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት ያገኙ ተቋማትን ስለማሳወቅ እና አቤቱታ ማቅረብን በተመለከተ በአዋጁ አግባብነት ባላቸው አንቀጾች በተደነገገው መሰረት ይሆናል።

## 24. የተሻረ መመሪያ

1) መስከረም 2003 የወጣው የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርት የዕውቅና አሰጣጥ መመሪያ በዚህ መመሪያ ተሻሽሏል።
2) ከዚህ መመሪያ ጋር የማይጣጣሙ ማንኛውም ሕጎች ተፈጻሚ አይሆኑም።